በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት

Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

መጋቢት 21 ቀን 2011
አዲስ አበባ

# 66ኛ መደበኛ የካቢኔ ዉሳኔዎች

የሚኒስትሮች ም/ቤት በዛሬው ዕለት ባካሄደው 66ኛ መደበኛ ስብሰባ የነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች አቅርቦትና ስርጭት ተቆጣጣሪ ባለስልጣን ማቋቋሚያ ረቂቅ አዋጅ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ አሳልፏል፡፡

ነዳጅ ለሀገር ልማትና ብልጽግና ወሳኝ የሃይል ምንጭና ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ወጥቶበት ወደ ሀገር ውስጥ የሚገባ ስትራቴጂካዊ ምርት ነው፡፡ በመሆኑም ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶች ደረጃቸውን በጠበቀ ሁኔታ በሰው ጤና፣ በንብረትና በአካባቢ ላይ ጉዳይ በማያደርስ መልኩ ስራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤ ግብይቱም ተገቢ በሆነ የንግድ አሰራር መመራቱን እና ለህብረተሰቡ ተደራሽነቱን ለማረጋገጥ ነዳጅና የነዳጅ ውጤቶችን በማጣራት፣ በማቅረብ፣ በማከማቸት፣ በማጓጓዝ፣ በማከፋፈል፣ በመቸርቸር እና ከነዚህ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ተግባራት የሚቆጣጠር ባለስልጣን ማቋቋም በማስፈለጉ የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ረቂቅ አዋጅ አዘጋጅቶ ለሚኒስትሮች ም/ቤት ውሳኔ አቅርቧል፡፡

ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ በስፋት ከተወያየ በኋላ ማሻሻያዎችን በማከል ተቀብሎ ይጸድቅ ዘንድ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲተላለፍ ወስኗል፡፡

//